# የአክራሪነትን አከርካሪ የሰበረው የመጅሊሱ ምርጫ

*ኢ.ብሳ ነመራ*

ከኢትዮጵያውያን ሙሥሊሞች ጋር በተያያዘ ኃይማኖቱን በበላይነት የሚመራው የእሥልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) አባላት ተነስተው በምትካቸው ይመረጡ የሚለው ጉዳይ ከሙሥሊሞች አልፎ የተቀሩትን ኢትዮጵያውያን ከሳበ ወራት ተቆጥረዋል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ አወሊያ መስጊድ አካባቢ ጥያቄው ከረር ያለ መልክ ይዞ እንደነበርም እናስታውሳለን፡፡

አወሊያ መስጊድ ይህንኑ የመጅሊስ ምርጫ እንዲካሄድ ለማድረግ በሚል 17 ሰዎችን የያዘ ኮሚቴ ተቋቁሞም እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ይህ ኮሚቴ ከመጅሊሱ ምርጫ ጋር አያይዞ ሰፋ ያሉ ጥያቄዎች አንስቶ ጉዳዩ የራሱ የሙሥሊሙ ብቻ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ መንግሥት ምላሽ ይስጥበት በሚል በተለይ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ጋር ተወያይቶም ነበር፡፡

ከመጅሊሱ ምርጫ በተጨማሪ ይኸው ኮሚቴ በተለይ "አህባሽ የተባለ የእሥልምና አስተምህሮ በግዳጅ እየተሰጠ ነው፤ ይህ እንዲቆም ይደረግ" የሚል ጥያቄ አንስቶም ነበር፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የመንግሥት ተወካዮች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የመጅሊስ አባላት ምርጫ በተመለከተ አባላቱ በተወሰነ ጊዜ በምርጫ የሚሰየሙ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ጉዳዩ የሙሥሊሙ ኅብረተሰብ ቢሆንም ጥያቄው ተገቢ ነው፣ የመጅሊሱ ምርጫ ይካሄድ ከሚለው ጉዳይ ከስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

"አህባሽ የተባለውን አስተምህሮ በግዳጅ መሰጠቱ ይቁም" በሚል በተነሳው ጥያቄ ዙሪያም መንግሥት ማንም በአስገዳጅነት አንድ ኃይማኖት ወይም አስተምህሮ ሌሎች ላይ መጫን እንደማይችል፣ ሆኖም ሰዎች በራሳቸው ፍቃድ የፈለጉትን ኃይማኖት ወይም አስተምህሮ የመከተል መብት እንዳላቸው በማስታወስ በግዳጅ የሚሰጥ አስተምህሮ እንደማይኖር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

"በግዳጅ እየተሰጠ ነው" በሚል ተቃውሞ የቀረበበትን አስተምህሮ በተመለከተ የእሥልምና ኃይማኖት ሊቃውንት - የዑለማዎች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሰጥ ከነበረው ነባር የእሥልምና አስተምህሮ የተለየ የእሥልምናን ኃይማኖት የሚፃረር አስተምህሮ እየተሰጠ እንዳልሆነ አረጋግጠ በይፋ መግለጫ መስጠቱም ይታወሳል፡፡ በግዳጅ እንዲማር የተደረገ ሰው አለመኖሩንም በትምህርቱ ፕሮግራሞች ላይ የታደሙ፣ ትምህርቱን የተከታተሉም፣ አንፈልግም ብለው ጥለው የወጡም አረጋግጠው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ "የሙሥሊሙ የመፍትሄ አፈላላጊ" በሚል ራሱን ሰይሞ በአወሊያ መስጊድ አካባቢ የሚንቀሳቀሰው ኮሚቴ መግባባት የተደረሰባቸው ጉዳዮች በተለይ የመጅሊሱ ምርጫ በሠላም እንዲካሄድ ማገዝን አልመረጠም፡፡ ከዚህ ይልቅ ውሉ የማይታወቀውን ተቋውሞውን አሟሟቀ፡፡ ራሱ ቡድኑ የሚያንቀሳቅሳቸው በእሥልምና ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ጥቂት ጋዜጦችና መፅሔቶችም ሙቀቱን ያራግቡት ያዙ፡፡

በተለይ የአወሊያ መስጊድ በየሣምንቱ ዓርብ የዚህ ቡድን የረብሻ ዓላማ መቀስቀሻና መምሪያ ማዕከል ሆነ፡፡ ይኼኔ የዚህ ቡድንና የተከታዮቹ አካሄድ የኃይማኖት መቻቻልን መንፈስ፣ የዜጎችን የመረጡትን ኃይማኖት የመከተልና የአምልኮ ሥርዐትን የመፈፀም ሕገ መንግሥታዊ መብትና ነፃነትን የሚፃረር የአክራሪነት ዘመቻ መሆኑ ገሃድ ወጣ፡፡  ይህ ቡድን የሚያራምደው አክራሪነት በ25 ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ኢሥላማዊ መንግሥት መመሥረት አለበት የሚል በውጭ ኃይሎች ድጋፍ የሚመራ ሥውር የፖለቲካ አጀንዳ ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎ መንግሥት የቡድኑ አካሄድ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር መሆኑን በማስታወስ ቡድኑ የተቀመጠለትን ቀይ መስመር ተላልፎ ሕግ እየጣሰ መሆኑን አሳሰበ፡፡

ይሁን እንጂ ለወራት ያህል እንደፈለገ ሲፈነጭ ዝም የተባለው ቡድን የልብ ልብ ተሰምቶት ማሳሰቢያውን ከምንም ሳይቆጥር በአክራሪነት እንቅስቃሴው ገፋበት፡፡ ይህ ፅንፈኛ ቡድን፣ ፅንፈኝነትን በመቃወምና በመዋጋት በሚታወቀው የአሜሪካ መንግሥት በጀት በሚተዳደረው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚያንቀሳቅሱት የአሜሪካ ድምፅ የአማርኛ ፕሮግራም የአይዞህ ባይነት ስሜታቸውን በሚያሳብቅ አኳኋን አጀንዳውን በማጋጋል የበለጠ የልብ ልብ እንዲሰማው አድርጓል፡፡ በነገራችን ላይ ራሱ የአወሊያው ቡድን ከሚመራቸው ጋዜጦች ውጭ የአገር ውስጥ የግል ሚዲያዎች የአክራሪውን ቡድን እንቅስቃሴ አላጋጋሉም፡፡ ይህን እንቅስቃሴ በማጋጋል ረገድ የአሜሪካን ድምጽ ራዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም  ታሪክ በፀያፍ ምግባር ሲያስታውሰው ይኖራል፡፡  ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያውያን ላይ ተቃውሞ ያነሳ ማንኛውንም ወገን  ሰይጣንም ቢሆን አይዞህ ከማለት የማይመለሱ እዚያው አሜሪካ ከሚኖሩ ቡድኖችና በእነዚህ ቡድኖች ከተወናበዱ ጥቂት ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያለፈ ለአወሊያው ቡድን ብርታት ለመስጠት የሞከረ የለም፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ ከሁለት ወር በፊት በእሥልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በቅዱስ ወርነት የሚታሰበው የረመዳን ፆም መግቢያ ላይ የአወልያው ቡድን ከመላ አገሪቱ አደናግሮ በደጋፊነት ያሰለፋቸውን የዋህ ሙሥሊሞች አሰባስቦ የመጀመሪያውን የረብሻ ዘመቻ አወጀ፡፡

በዚህ ጊዜ የአወሊያው ቡድን ዓላማውን አስታጥቆ ባሰማራባቸው ጥቂት የአዲስ አበባ መስጊዶችና የቡዱኑ ዋና ማዕከል በሆነውን አወሊያ መስጊድ ከእሥልምና ኃይማኖት ሥርዓት ውጭ ካለ ወቅቱ ሙሥሊሞች ወደመስጊድ እንዲወጡ ታወጀ፡፡ ይኼኔ አስቀድመው የተዘጋጁት ደጋፊዎቻቸው እኩለ ሌሊት ገደማ ለረብሻ ወጡ፡፡

በዚህ ጥሪ መሠረት ከቤታቸው የወጡ ጥቂት ሙሥሊም ወጣቶች የሠላማዊ ሙሥሊሞችን በር እያንኳኩ “ጀሃድ ነው ውጡ” እያሉ ቢቀሰቅሱም የረብሻ ዓላማቸውን የሚያግዝ ሙሥሊም ማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ወጣቶቹ ፀጥታ በማስከበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ፖሊሶች ላይ ድንጋይ በመወርወር ጥቂት ፖሊሶች ላይ የመፈንከት አደጋ ከማድረስ ውጭ ምንም ውጤት ሳያገኙ ተበተኑ፡፡ ይህን ተከትሎ በዘጠኙም የአገሪቱ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ የሚገኙ ሙሥሊሞች የአክራሪውን ቡድን አካሄድ በመቃወም ቁጣቸውን በሠላማዊ ሰልፍ ገልፀዋል፡፡

መንግሥትም ከዚህ ረብሻ ጀርባ ያሉ ሰዎችን አጣርቶ በቁጥጥር ሥር አዋለ፡፡ በዚህም ራሱን የሙሥሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ በሚል ራሱን የሰየመው ቡድን አባላት በቁጥጥር ሥር ውለው በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

በዚህ አኳኋን ቅዱሱን የረመዳን ወር፣ ሰይጣናዊ የሆነ ረበሻ የሚካሄድበት ወር ለማድረግ የታለመው የአክራሪዎች ሴራ ከሽፎ ሙሥሊሙ ፆሙን በሠላም አጠናቆ እንደወትሮው በነቂስ አደባባይ ወጥቶ በሚያካሂደው ልዩ የበዓል የፀሎት ሥነ ሥርዓት በዓሉን አክብሮ በሠላም ወደ ቤቱ ገባ፡፡

የሙሥሊሙ ጥያቄ የነበረው የእሥልምና ጉዳዮች ምክር ቤት - መጅሊስ አባላትን የመምረጡ ሂደት ቀጠለ፡፡ ይህ ምርጫ አይቀሬ መሆኑንና ሥውር ዓላማውን ለማራመድ የሚያነሳው ሕጋዊ ሽፋን ያለው አጀንዳ እንደሚያሳጣው የተረዳው አክራሪ ቡድኑ መቃወሚያ ሰበቦችን አበጀ፡፡ ይህም ምርጫው በቀበሌ ሳይሆን በመስጊዶች ውስጥ መካሄድ አለበት የሚል ነበር፡፡

ይህን አስመልክቶ በሥራ የነበረው የእሥልምና ጉዳዮች ምክር ቤት፣ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የእሥልምና ጉዳዮች አወቃቀር ቀበሌን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ምርጫው በቀበሌ ደረጃ መካሄድ እንደሚገባው አስታወቀ፡፡ የእሥልምና ሊቃውንት - ዑላማዎች ምክር ቤትም ኃይማኖታዊ ምክንያቶችን ጠቅሶ ምርጫው ከመስጊድ ውጭ በሆነ ቦታ መካሄድ እንዳለበትም ገለጸ፡፡

በዚሁ መሠረት መስከረም 20፣ 2005 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ሙሥሊሞች በየሚኖሩበት ቀበሌ በተዘጋጀላቸው ቦታ ተሰባስበው በነፃነት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አስመራጮችንና የምርጫ ታዛቢዎችን መረጡ፡፡

ይህን ተከትሎ ምርጫው ሊካሄድ ሁለት ቀናት ሲቀሩት ዓርብ በተለይ በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ ለፀሎት የወጡ አክራሪው ቡድን ያጠመቃቸው ሙሥሊሞች፣ ቢጫ በማሳየት ተቃውሟቸውን ገለፁ፡፡  የቢጫው ወረቀት ምንነትን አስመልክቶም “ለመንግሥት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው” የሚል ወሬ ተሰማ፡፡

አስመራጮቹንና የምርጫ ታዛቢዎቹን መርጦ የእሥልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላትን ለመምረጥ በዝግጅት ላይ የነበሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በመላው ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሙሥሊሞች ግን ቢጫውን ወረቀት “አክራሪው ቡድን ለራሱ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ነው” በሚል ከምንም ሳይቆጥሩ እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ምርጫውን አካሄዱ፡፡

ምርጫው የተካሄደው ለምርጫ የተሰባሰቡት ሙሥሊሞች በቀጥታ በዚያው በምርጫው ቦታ ከጠቆሟቸው ዕጩዎች መካከል ነው፡፡ እጩዎቹ የራሳቸውን ወኪል ለመምረጥ የወጡ እንጂ እንደሚመረጡ አስቀድመው የሚያውቁ አልነበሩም፡፡ በአንዳንድ የምርጫ ቦታዎች፣ የታጩበት ኃላፊነት ከባድ በመሆኑ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን በመግለጽ ከእጩነት እንዲነሱ የጠየቁ ነበሩ፡፡ መራጭ ሙሥሊሞች ይህን የእጩዎቹን ጥያቄ የተቀበሉበት ሁኔታ ያለውን ያህል “የለም እርስዎን ነው የምንፈልገው ብለው” እጩነታቸውን አፅንተው የመረጡበትም ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

ሁኔታው ምርጫው ከሙሥሊሙ ማኅበረሰብ ፍላጎት ውጭ በሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ተፅዕኖ ሊደረግበት ያልቻለ ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ እንደነበረ ያረጋግጣል፡፡ ይህ በመላው ኢትዮጵያ ከ7 ነጥብ 5 ሚሊየን በላይ ለአካለ መጠን የደረሱ ሙሥሊሞች በቀጥታ የተሳተፉበት ምርጫ ለአክራሪው ቡድን ጠንከር ያለ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

በኃይማኖት ሽፋን ሥውር ዓላማን ለማሳካት የአመፅ መንገድ የማይቀበል መሆኑ ቀጻሚው መልዕክት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውጭ ሆነው የገንዘብ ድጋፍ እያደረጉ ርዕዮተ ዓለማዊ ዓላማቸውን ለማሳካት ለሚሞክሩ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያ አክራሪነትን የማትሸከም አገር መሆኗን በግልፅ አሳውቋል፡፡

ማንኛውም አመፅ ቀመስ እንቅስቃሴ የመንግሥት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል በሚል ቀቢፀ ተስፋ ካሁን ካሁን “መንግሥት በኃይል ተገለበጠ” በሚል ቅዥት ለሚናውዙ ጥቂት በውጭ አገራት ለሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሠላሙ ላይ የማይደራደር መሆኑንም አስተምሯል፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን መብታቸውን ጠንቅቀው ማወቃቸውንና ዴሞክራሲያዊ ባህል ማዳበራቸውንም በግልፅ ያሳየ ምርጫ ነው፡፡

እናም የአክራሪውን ቡድንና የኢትዮጵያን ሠላም ያናጋልኛል ብለው ሊንጠለጠሉበት የሞከሩ ቡድኖችን አከርካሪ ሰብሮ ያሽመደመደ እርምጃም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ የሚያስገርም ወሬ ሰምተናል፡፡ ይህም የመጅሊሱ ምርጫ ከመካሄዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ከታህሳስ ወር ጀምሮ መቀመጫውን አወሊያ መስጊድ አድርጎ አመፅ ለመቀስቀስ ሲወራጭ የነበረውን ቡድን ሲመሩ የነበሩና በዚህ የአመፅ እንቅስቃሴ ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር ውለው ጉዳያቸው ፍርድ ቤት የቀረበ ግለሰቦች በጠበቃቸው አማካይነት “የምርጫው ሂደት ሕገወጥ ስለሆነ እንዳይካሄድ ይታገድ” በሚል ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ ነው፡፡

እርግጥ ማንኛውም ግለሰብ ይመለከተኛል የሚለው ጉዳይ ላይ ተገቢ ያልሆነ ወይም ህገ ወጥ የሆነ ጉዳይ አለ ብሎ ሲያምን ይህ እንዲታረም ለፍርድ ቤት ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል አቤት የማለት መብት አለው፡፡ በመሆኑም ግለሰቦቹ ይህን ማድረጋቸው በራሱ እንደ ጥፋት ላይቆጠር ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ አጠቃላይ የምርጫውን ሂደት እንዲሁም ግለሰቦቹ ከተቀሩት በ30 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሙሥሊሞች በተለየ ይህን አቤቱታ የማቅረብ መብት አለን ብለው ማሰባቸው ብዙዎችን እጅግ በጣም አስገርሟል፡፡ አመፅ በመቀስቀስ ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉት ግለሰቦች በሠላም ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሙሥሊሞች ያደረሱባቸውን አሳፋሪ ሽንፈት ላለመቀበል ያደረጉት የመጨረሻ ሙከራ ነው፡፡

በሠላም ወዳድ ሙሥሊም ኢትዮጵያውያን የደረሰባቸው ሽንፈት ለኅመዘዛቸው ጥቂት አጋፋሪዎቻቸው “አይዟችሁ አሁንም አለን” የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ የተደረገ በሽንፈት ከወደቁበት ለመቀስቀስ የተወሰደ እርምጃ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን ጉዳዩ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በማድረግ ቀጠሮ በሚኖሩባቸው ቀናት

የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ /ቪ.ኦ.ኤ/ን የመሰሉ አጫፋሪ ሚዲያዎች ጉዳዩን እያራገቡ ትንፋሻቸው የሚቋረጥበትን ጊዜ ለማራዘም ያግዘናል በሚል እሳቤ የተደረገ ከመሆን ውጭ አይደለም፡፡

ይህ የአወሊያ መስጊዱ ቡድን በአዲስ አበባ አንድ ጥግ በሚገኝ መስጊድ ዙሪያ ባሉ ከአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም አነስተኛ ሙሥሊሞች የሚያውቁት ቡድን ነው፡፡ በዚህ መስጊድ ደረጃም ቢሆን በሕጋዊ መንገድ ውክልና የተሰጠው አይደለም፡፡ "የሙሥሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ" የተሰኘው የአወሊያ ቡድን የራሱን ቡድናዊ ተልዕኮ ይዞ ራሱን የሾመና ፖለቲካዊ ዓላማ ባላቸው ውጭያዊ አካላት  የሚደገፍ፣ በርቀት መቆጣጠሪያ የሚሾር ቡድን ነው፡፡

ይህ ራሱን የሰየመ ወይም ከውጭ የተሰየመና ተልዕኮ የተሰጠው ቡድን በመላው አገሪቱ የሚገኙ ቡድኑን ከነመኖሩም የማያውቁ ሙሥሊሞችን ወክሎ መጅሊሳችሁን ለመምረጥ መነሳታችሁ ሕገ ወጥ ነው፡፡ የማለት የሕግም የሞራልም መብት የለውም፡፡ ያም ሆነ ይህ ሠላማዊ ሙሥሊሞች ከዚህ ቀደም ሰምተውትም አይተውትም በማያውቁት አኳኋን በብዛትና በንቃት ተሳትፈው የመጅሊስ አባላትን ምርጫ አካሂደዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የአወሊያው ቡድን ደጋፊዎች ናቸው የተባሉት በቢጫ ካርድ  ማስጠንቀቂያውን ያሳዩት፣ ለአብላጫው ሠላማዊ ሙሥሊም ኢትዮጵያውያን ሳይሆን፣ ጥቂት የተለየ ዓላማ ላላቸው የአወሊያው ቡድን አባላት ነው ማለት ያስደፍራል፡፡